# የሱዛን ከሚንግስ ራእይ

The Vision of Susan Cummings
On January 31, 2003

እ.ኤ.አ. በጃንዋሪ 31፥2003 ዓ.ም

ዛሬ፥ ለአንድ ጓደኛዬ የአምልኮ ቀለበትን (worship hoop) እየሠራሁ ሳለ፥ ጌታ ራእይ ሰጠኝ፥ እናም ጌታን እያመለኩት ሳለ፥ ስለራእዩ ተናገረኝ። እንድትመረምሩት ለጸሎት ለእናንተ እተወዋለሁ። ያሳየኝ ይህ ነው፦

ወንበር ላይ ተቀምጫለሁ፥ እናም በድንገት ጌታን የግድ ማምለክ እንዳለብኝ ተሰማኝ። እያመለኩ ሳለ፥ ወደ ላይ ተነጠቅሁ፥ እናም ወደ ማላውቀው ቦታ በመንፈስ ተወሰድሁ። ከዚህ በፊት ሆኜበት የማላውቀው የተለየ አካባቢ ነው። የገባሁበትን ሕንጻ አየሁ፥ እናም በመተላለፊያው (ኮሪዶር) ላይ ቆሜ ነበር። ይህ መተላለፊያ ኮሪዶር ወደ ሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች ይሄዳል፥ እንዲሁም ረዥምና ቀይ ምንጣፍ የተነጠፈበት ነው። በመተላለፊያው ኮሪዶር ብዙ በሮች ይገኛሉ። ሆኖም ግን ሁሉም በሮች የተለያዩ ናቸው። ረጃጅም በሮች፥ አጫጭር በሮች፥ የእንጨት በሮች፥ የብረት በሮች፥ የመስታወት በሮች፥ እንዲሁም የተቆለመሙ በሮች፥ ብዙ ብዙ፥ ሁሉንም ለመግለጽ በጣም ብዙ ናቸው። በዚህ ቦታ እነዚህን ሁሉ የተለያዩ በሮች ማየት ያስቃል። ይሄ እንደዚህ መሆኑ ያልተለመደ ነው ብዬ እያሰብሁ ነበር፥ ድምጽ የሰማሁት። በመተላለፊያው ወደላይና ወደታች ተመለከትሁ፥ ድምጹ ከየት እንደመጣ እየፈለግሁ ነበር። በኮሪዶሩ ወደታች በቀኝ በኩል መውረድ ጀመርሁ። በዚህ መተላለፊያ መብራቱ ደማቅ አልነበረም፥ ደብዛዛም ግን አልነበረም። ምንም የሚታይ መብራት አልነበረም፥ ሆኖም ግን ይታያችኋል። በበሮቹም ላይ ደግሞ የበር እጀታ እንዳልነበረ አስተዋልሁ። ሁሉም በር ተዘግቶ የነበረ ሲሆን እያንዳንዱ የራሱ የሆነ መግቢያ መንገድ አለው። ድምጹ መተላለፊያውን ተከትሎ ይሰማል፥ እኔም ድምጹን ተከትዬ እየተጓዝሁ ነው። ምንጣፉ ቀይ እንደነበር አስተዋልሁ፥ ነገር ግን ደግሞ በጣም አርጅቷል። በምንጣፉ ላይ የመንገድ ቅርጽ አለ፥ እናም ይህ ቦታ በተደጋጋሚ የተሄደበት እንደሆነ ግልጽ ነው። ምንጣፉ ምንም ያረጀ ቢሆንም ለማየት የሚጋብዝና የሚያስደስት ነበር። ሲራመዱበት ይመቻል። መሄዴን ስቀጥል፥ መታጠፊያ ጋር ደረስሁ። ተመለከትሁ፥ ነገር ግን ማንንም አላየሁም፥ ወይም ደግሞ ከሌላኛው መተላለፊያ ምንም ድምጽ አልሰማሁም፥ ስለዚህ እርምጃዬን ቀጠልሁ።

ወዲያው፥ የሆነ ሰው ከፊቴ ካለ በር ፊት ቆሞ አየሁ። በእጁ ሰይፍ እንደያዘ በበሩ ፊትለፊት ቆሞ ነበር። ድምጾቹ ከዚያ በር በስተጀርባ የሚመጡ ይመስላሉ። ወደ ሰውዬው እንዳልሄድ የሆነ ፍርሀት ተሰማኝ፥ በሩን እየጠበቀ ሲታይ በጣም ኮስተራ (series) ይመስላል። ስጠጋ፥ ዞር ብሎ ተመለከተኝ። ከዚያም ሰው እንዳልነበረ አወቅሁ፥ በሩን የሚጠብቅ መልአክ ነበር። ያለመመቸት ይሰማኝ ጀመር፥ እናም ተመልሼ ከእርሱ መራቅ ጀመርሁ፥ ድንገተኛ ፍርሀት ስለተሰማኝ ሞኝ መስዬ ልታየው አልፈለግሁም።

ከዚያም መልአኩ ሰይፉን ዝቅ አድርጎ ወደ እኔ ጠቆመው። "*ማንን ትፈልጊያለሽ?*" አለኝ። መንቀጥቀጥ ጀመርሁ ለምን በዚያ እንደሆንሁ እንደማላውቅ ነገር ግን ጌታ እንደጠራኝ ነገርሁት። ከዚያም መልአኩ ፈገግ አለ፥ ቀረብ ብሎም ተመለከተኝ፥ ከዚያም "*አዎን፥ ጠርቶሻል*" አለኝ። ከዚያም ወደ ጎን ፈቀቅ አለና በበሩ እንድገባ አመለከተኝ። በሩም ከዚያ ማንም ሳይነካው ተከፈተ። ወደ ክፍሉ ስገባ እፎይታ በውስጤ ጎረፈ። እዚህ ለማየው ነገር ዝግጁ አልነበርሁም። ግርግዳው በሙሉ (የቦታ) ካርታዎች የተሞላበት ክፍል ውስጥ ገባሁ። የወረቀት ካርታዎች ግን አልነበሩም፥ ነገር ግን በግርግዳው ላይ የሆነ ቦታ የተቀመጡ እውነተኛ ስፍራዎች ነበር የሚመስሉት። ሁሉም አህጉር በዚያ አለ፥ እንዲሁም ሁሉም ሀገራት። ባሕሮች፥ ውቅያኖሶች፥ እንዲሁም ወንዞቹ። ሁሉም በዚያ ነበሩ፥ በሁሉም ግርግዳዎች ላይ። በእይታው በጣም ተገርሜ ነበር፥ በግርግዳዎቹ ላይ ማን አስቀመጣቸውም ብዬ አሰብሁ። ሁለት ወንበሮችንም በክፍሉ ውስጥ ማየት እችል ነበር፥ እንዲሁም በወንበሮቹ አጠገብ በመስመር የቆሙ ሰዎች። በወንበሮቹ አንድ ሰውና ጌታ ተቀምጠው

ነበር። ሰውዬውና **ጌታ** ይነጋገሩ ነበር። ከዚያም እነዚህ በመተላለፊያዎቹ የሰማኋቸው ድምጾች እንደሆኑ አስተዋልሁ። ጮኽ ብለው ሳይሆን በእርጋታ ይነጋገሩ ነበር፥ ከዚያም እንዴት ታች መተላለፊያው ድረስ ልሰማቸው እንደቻልሁ አሰብሁ። በመስመር የነበሩት ሰዎች ወደ **ጌታ** አንድ በአንድ ሲመጡ አስተዋልሁ። በመስመር የነበሩ ወንዶችም ሴቶችም ነበሩ። እያንዳንዳቸው ከ**ጌታ** አጠገብ ቆመው ይነጋገሩት ነበር። **ጌታም** ወደ ካርታዎቹ ይጠቁምና፥ በሀገራቱ ላይ ስለሚከሰቱ የተወሰኑ ጉዳዮች ይናገራል፥ እናም ለዛ ሰው የሚሆነውን ያሳያል። እኔ እያየሁ፥ **ጌታ** ወደ አንድ ሀገር ጠቆመ፥ ከዚያም እሳት በሀገሪቱ መሰራጨት ጀመረ በምድሪቱም ያሉትን እጽዋት ሁሉ ፈጃቸው (በላው።) ይህን ሳይ በጣም ፈራሁ። እሳቱን ሊያቆም የሚችል ማንም ሰው አልነበረም። ከ**ጌታ** ጋር ቆሞ የነበረው ሰው ተመለከተና ራሱን ነቀነቀ፥ መስመሩንም ለቀቀ። ራሱን አቀርቅሮና እጆቹን አቆላልፎ ሲሄድ አየሁት። **ጌታ** ያዘነ ይመስላል፥ ሲሄድም ተመለከተው።

ከእኔም ቀድማ አንዲት ሴት ወደ **ጌታ** ቀረበች፥ ከ**ጌታም** አጠገብ ቆመች። **ጌታ** ወደ ውቅያኖሶቹ ጠቆመ እናም በታላቅ ማእበል ይታወኩ ጀመር። ማእበሉም ግዙፍ ሞገድን ሠራና ከአንዳንድ የየብስ አካላት ጋር ተጋጨ፥ በውቅያኖሶቹም ላይ ከታላላቆቹ ሞገዶች የተነሳ መርከቦች ሲሰምጡ አየሁ። እያየሁም ማእበሉ ከባድ ከመሆኑ የተነሳ የሞገዱ ጩኸት እጅግ አስፈራኝ። እኔ ከቆምኩበት ቦታ እንኳን ማእበሉ ሲጋጭ የሚሰማ ያህል ተሰማኝ። ሴቲቱ ምንም ዓይነት ስሜት አላሳየችም። ተገረምሁ። ተመለከተችና፥ ምንም ለውጥ የለውም አለች፥ ሰዎቹ እንደሆነ ሞተዋል። ከዚያ ወደ ኋላ ተመለሰችና ለመሄድ ፊቷን አዞረች። አስቆምኳት፥ እጇንም በትከሻዋ ላይ ጫንሁት። አንገራገረች፥ ከዚያም ጉዞዋን ቀጠለች። **ጌታ** ስትሄድ አያት፥ በዓይኖቹም ውስጥ ሀዘን ነበር፥ በዚያም ልመለከተው የማልፈልገው ህመም። በሆነ መልኩ ተጠያቂነት ተሰማኝ። ከዚያም የእኔ ተራ እንደደረሰ ተረዳሁ። ተጠጋሁና ከ**ጌታ** አጠገብ ቆምሁ። ምን ማድረግ እንደነበረብኝ እርግጠኛ አልነበርሁም፥ ነገር ግን **ጌታ** አጠገቤ ስለቆመ ደኅንነት ተሰማኝ። ሁኔታዬን አስተዋለና በትንሹ ፈገግ አለ። ከዚያም እጁን አንሣና ከፊታችን ራቅ ብሎ ወዳለው ግርግዳ እጆቹን አመለከተ። ግርግዳው በታላቅ መንቀጥቀጥ ወደ ህያውነት መጣ። ሙሉ ግርግዳውና ምድሪቱ ሁሉ የተንቀጠቀጠ ነው የሚመስለው። ከቆምኩበት ቦታ መንቀጥቀጡ ይሰማኝ ነበር፥ እናም አስፈራኝ። **ጌታን** ያዝሁት፥ እናም መሬቶቹ በኃይል ሲንቀጠቀጡ ተመለከትሁ። ታላቅ ድምጽ ነበር፥ ከዚያም እርጋታ ሆነ። ከመንቀጥቀጡ የተነሳ መሬቶቹ ተከፋፍለዋል፥ እናም የሞት ጸጥታ ነበር። በጣም ረጭ ያለ ነበር። ወደ **ጌታ** ተመለከትሁ፥ **እርሱ** ግን ግርግዳውን እየተመለከተ ቀረ። ደግሜ ተመለከትሁ፥ እናም ከምድሩ በጣም ጥቂት ያልተነኩ ስፍራዎችን አየሁ። ምንም የሚታወቅ እስኪጠፋ ነበር የተንቀጠቀጠው። ከዚያም አንዱ ተራራ ሲፈነዳና የእሳት ፈሳሽ ወደ አንዳንድ የምድሩ ክፍሎች ሲተፋ አየሁ፥ ከዚያም በድጋሚ ተንቀጠቀጠ። ሰዎቹ በየአቅጣጫው ይሮጡ ነበር መሮጫ ግን አልነበረም። የእሳቱ ፈሳሽ ባረፈባቸው የምድሩ ክፍሎች እሳት ይቀጣጠላል ምድሪቱንም እንደ ችቦ ለኮሳት። የተቃጠለው መሬት ይሸተኝ ነበር። ከዚያም ድካም ተሰማኝ፥ እናም ለመቀመጥ ፈለግሁ። **ጌታም** ከአጠገቡ አስቀመጠኝና ተመለከተኝ። ከዚያም ያየሁትን ተረድቼው እንደሆነ ጠየቀኝ።

ክፍሉ ውስጥ ከገባሁ ጀምሮ ያየኋቸውን ሁሉ ግምት ውስጥ አስገባሁ። ለ**ጌታ** **እርሱ** እንደጠራኝ እንደማውቅ ነገርሁት፥ ነገር ግን ለምን እነዚህን ድርጊቶች እንዳሳየኝና ሰዎቹ ለምን በዚያ እንደነበሩ እንደማላውቅ ነገርሁት። ከዚያም **ጌታ** እንዲህ አለ፡ "*ይህ የእኔ የካርታ ክፍል ነው።*

*የምድርን መሠረቶች የነደፍሁት እዚህ ነው፥ ገና ከመፍጠሬ አስቀድሞ። ከመጀመሪያው ጀምሮ የሆነው ሁሉ፥ እስከዚህች እለት ድረስ አይቼዋለው አከናውኜውማለሁ። በምድር ላይ ምንም ነገር ያለ እኔ ቅድመእውቀት ወይም የበላይ ፈቃድ አይሆንም። ለሰው ምድርን ልፈጥርለት መረጥሁ፥ አብረን በጋራ እንሆንበት ዘንድ። መኖሪያ ስፍራዬ ሁልጊዜም ከሰው ጋር ነበር፥ ነገር ግን ሰው ገፋኝ፥ እናም ከእኔ ተለይቶ መኖርን መረጠ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፥ በዝቅተኛው ሰፊ ስፍራ ያለ እኔ ኖሩ፥ እንዲሁም እጄ በጉዳዮቻቸው ሳትመራቸው። በዚህ ቀን እዚህ ያየሽው፥ የትውልዶችን መጨረሻና የምርጫዎቻቸውን ውጤት ነው። እውነቱ ከእንግዲህ ኃጢአቱን ሊሸፍነው አይችልም፥ እናም ሊያጋልጠው ይታገላል።*

*በዘመናት ውስጥ፥ ሰዎችን ወደዚህ እንዲመጡና ይህን ክፍል እንዲያዩ ጠርቻቸዋለሁ። በዚህ ነው በሰው ምርጫ ምክንያት የሚመጣውን ታላቅ ሀላፊነት የማሳያቸው። እንዲሁም ደግሞ ልቦች የሚገለጡትና በውስጣቸው ያለው የሚታየውም በዚህ ነው። አየሽ፥ ወደ ሕዝቤ እጣራለሁ፥ ነገር ግን እነርሱ ወደ እኔ አይመጡም። የሚመጡት ጥቂቶቹም፥ እነርሱም በካርታዎቹ ላይ ባሉት ምድሮች ላይ ላሉት ለመድረስ ሸክሜን ለመሸከም አልያም ላለመሸከም ይመርጣሉ። ብዙዎች ምላሽ ላለመስጠት፥ ግድ ላለመሰኘት ይመርጣሉ። ስለ ግል ደኅንነታቸውና ምቾታቸው የበለጠ ይጨነቃሉ፥ የግል ህይወታቸውንና ነፃነታቸውን አደጋ ላይ ሳይጥሉ ለሌሎች ሊደርሱ አይችሉም። ለወንድማቸው ህይወታቸውን አደጋ ላይ መጣል አይችሉም፥ ስለዚህ ትተው ይሄዳሉ። ያየሽው ሰው በፍርሀት ተሞልቶ ነበር። ለእኔ ካለው መታዘዝ የተነሳ ነው የመጣው፥ ነገር ግን ፍርሀቱን በቁጥጥር ውስጥ አላዋለም (አላሸነፈም)፥ እናም ሙሉ በሙሉ በእኔ አልታመነም፥ (በእርሱ) ምድር ላይ እሳቱ ሲመጣ ሲያይ፥ እኔ እንድጠቀምበትም ሆነ እንድንከባከበው እንኳን አላመነኝም። ከውጭ መልካም ይመስላል፥ በደኅንነቱ ላይ የእውነት ፈተና ለሆነው ነገር ሲጋለጥ፥ አፈገፈገ፥ እየተጎዱ ላሉት ሊደርስላቸው አልቻለም። ጥፋቱን ብቻ ነው ያየው፥ የሰዎቹን መሻት ማየት አልቻለም። ስለዚህም ወደ ራሱ ጥፋትና ድርሻ ሄደ። በዚህ የነበረችውም ሴት እንዲሁ በስጋት ተሞልታ ነበር። አውሎንፋሱ የ(እርሷን) ከተማዋን ሲበታትነው አይታ ልቧን አደነደነች። በምድር ላይ ከእርሷ ጋር እንድጓዝ፥ አጋሯም እንድሆን አልፈቀደችልኝም። ያለ እኔ ጸጋ በምድር ላይ በህይወቷ ተንገላታች፥ እናም ደንድናና ቀዝቅዛ ቀረች። የበዙት የጊዜው ኢፍትሐዊነቶች እኔ እንኳን እንደማስብላት አልያም ልረዳት እንደምችል ማመን እስኪያቅታት ድረስ እምነቷን ሸረሸሩት። በህይወቷ እያንዳንዱ የመጣባትን ሁሉ በህመም እየተቋቋመች ተራመደች እናም ተስፋ ቆረጠች። እርሷም ጭምር መጥታለች፥ ነገር ግን በመታዘዝ አይደለም የመጣችው፥ ነገር ግን ከመሻት የተነሳ ነው። በዚህ የሰላም አፍታ አግኝታ ነበር፥ ነገር ግን ያለ እኔ ወደ ህይወቷ ተመለሰች። በአውሎ ንፋሶቹ ውስጥ ምንም ተስፋ አላየችም፥ ስለዚህም ልትደርስላቸውና ማንንም ልትረዳ አልቻለችም። ያለ ምኅረትና ፍትህ የሆነን ሞትና ጥፋትን ብቻ አየች።*

*ከዚያም አንቺ በፊቴ መጣሽ። በምድርሽ ላይ የሚመጡትን አንዳንድ ነገሮች ላሳይሽ ወደዚህ አምጥቼሻለሁ። ታላቁ መናወጥ በገሀድ መሆን ገና መጀመሩ ነው፥ ነገር ግን በእርሱ ውስጥ ያለውን ልቤን እንድታውቂ አሳየሁሽ። በሀገሪቱ ላይ ስር የሰደደውን ኃጢአትና ጣኦት አምልኮ መንጭቆ ለማውጣት አስፈላጊ መናወጡ ነው። ከምድሩ በታች በብዛት ስር ሰድዶአል እናም ከመጀመሪያውም በዚያ ነበር። ነገር ግን እኔ ምድሪቱን እየጎበኘሁ ነው፥ ነፃም ይወጣ ዘንድ ይናወጣል። በምድርሽ ፍፃሜ ላይ ሲገነባ ከነበረው ታላቅ ጫና (ግፊት)ና ሲካሄድ ከነበረው ውጊያ የተነሳ ተራራው ፈነዳ።*

*በመናወጡ ጊዜ እኔን መያዝሽ ትክክል ነበርሽ፥ ያለው ብቸኛው ደኅንነት እርሱ ስለሆነ። ሊንቀጠቀጥ የሚችል ነገር ሁሉ፥ ይንቀጠቀጣል። ምንም ነገር እንደነበረ አይቀርም፥ ሊሆን አይችልም። የምድር ጩኸት አርነትን የትውልዶችም መታረድ ፍትህን ይጠይቃልና። ደሙ ከምድር በታች ይጮኻልና ከእንግዲህ ሊገታ አይገባውም። ሰው ወደ እኔ እንዲዘረጋ ጊዜ ሰጥቻለሁ። ሰው ሁሉ እውነቱን እንዲሰማ እድሉን ሰጥቻለሁ። እንዲድኑና እንዲያውቁኝ ሕይወቴን ሰጥቻለሁ፥ እንደዚያም ሆኖ እኔንና እውነቱን ላለመቀበል መረጡ።*

*ከእኔ ውጪ ምንም ነገር የለም፥ ከራሱ ከሰዓቱ በስተቀር። ሰዓቱ እንኳን ወደ ፍፃሜው እየመጣ ነው። ሊመጣ ያለውን ላሳይሽ ወደዚህ ጠርቼሻለሁ። ልብሽን ለመፈተን ወደዚህ ተርቼሻለሁ። ራስሽን ከደሽ ሄደሽ በምድር ላይ ለቀሩትና ሊመጡ ባሉት ቀናት መከራን ለሚቀበሉት ሕዝቤ ትደርሺላቸዋለሽ? ሕዝቤ የምለው፥ ሁሉንም ሰዎች እኔ ስለፈጠርኳቸው የእኔ ናቸውና ነው። ነገር ግን ልጆቼ አይደሉም፥ ሙሽራዬም አይደሉም።*"

"*ድካምሽን አሸንፈሽ በማንኛውም ዋጋ ቢሆን ትደርሺላቸዋለሽ? እኔን ሙሉ በሙሉ በመተማመን መቆም ትችያለሽ፥ በከባድ ፈተናቸው (ተግዳሮቶች) መሀል ሳታወላውዪ፥ እናም ፍቅሬን በዙሪያሽ ላሉት ልታሳዪ ትችያለሽ? ታላቁን ቀውስ (ምስቅልቅል) ስታዪ ድካምሽን አይቻለሁ። ለእኔ ያለሽን ትጋትሽንና ቅናትሽን*

*አውቃለሁ። በመስጠት **እኔን** እንደምትፈልጊና የበለጠም እንደምትሺኝ አውቃለሁ፥ አሁን ትቀጥያለሽ፥ በታላቁ ዋጋ እንደሚያስከፍልሽ እያወቅሽ? ሥጋ ከዋጋው የተነሳ ይታክታል፥ ነገር ግን በ**እኔ** ኃይል ተነስተሽ ከስርሽ ምርኩዝ እንድሆን ትፈቅጂያለሽ?*

*ብዙዎች የሚወድቁበት ምክንያት አብሬያቸው እንድመጣና እንድረዳቸው ስለማይፈቅዱልኝ ነው። የ**እኔን** እርዳታ እንደሚፈልጉ ሊቀበሉት አይችሉም። የድካም ምልክትና፥ ደካማም መሆን ያለመብሰል መስሎ ይሰማቸዋል። ሆኖም፥ ለራሳቸው እንኳን ለመድረስ ስህተታቸውን በበቂ ሁኔታ ማሸነፍ አይችሉም። ብዙዎች በሚመጡት ቀናቶች ይወድቃሉ፥ የሆነ ጊዜ እንድረዳቸው ፈቅደውልኝ የነበሩ፥ እናም ከእንግዲህ ወዲያ የማይፈልጉኝ መስሎ የተሰማቸው፥ እናም ያለ **እኔ** የተጓዙ። ያደጉና መጽናትን ያገኙ እናም አሁን ለሌሎች ምሳሌ የሆኑና የሰዎች መሪ እንደሆኑ ተሰማቸው። ሆኖም፥ የራሳቸውን ትምክህትና መውደቃቸውን እንኳን ማየት አልቻሉም። ብቻቸውን መጓዛቸውን ቀጠሉ፥ እናም ቀስ በቀስ እምነታቸውን አጡ፥ እንዲሁም ጥልቅ ፍቅራቸውን። ወዲያውም ለሌሎች ያላቸውን ክብር አጡ፥ እናም ትእቢተኛ ሆኑና የሚታገሉ ሌሎችን ይኮንናሉ። የሚከፈለው ታላቅ ነው፥ ዋጋውም ከፍ ያለ ነው፥ እንደዚያም ሆኖ መኸሩ ደርሷል እናም ጊዜው አጭር ነው። ብዙዎች ገና ጊዜ ያለ ይመስላቸዋል፥ እናም ንቁ ሆነው አይቆዩም፥ እናም **እኔን** እየፈለጉኝ አይደለም። ወደ ራሳቸው ፍፃሜ (ሞት) እየሄዱ ነው፥ የሚመራቸው የ**እኔ** ጥበብ የላቸውምና። **እኔን** በመሻት ፋንታ የራሳቸውን መንገድ መሄድን መርጠዋል። የዚህ ዓለም ሀሳብ ብዙዎችን ያታልላቸዋል፥ እናም ለመስማትና በልባቸው የደነዘዙ ይሆናሉ። ሌሎችም ያላቸውን ንቃት ያጣሉ ስለሆነም ነገሮች ሲለወጡ እንኳን አያስተውሉም፥ ልባቸው ከ**እኔ** በጣም ርቋልና። ብድራታቸውን ያገኛሉ።*

*ወደዚህ እንድትመጪና ወደፊት የሚሆነውን እንድታዩ ነው የጠራሁሽ። ብዙዎች ታማኝ ነቢያቶቼ አስቀድሞ እዚህ መጥተው ነበር፥ እናም አሁን የማንቂያውን ደውል እያሰሙ ነው። ብዙዎች ሌሎች ለመድረስና የ**እኔ** የሆኑትን ለመጥራት የታመኑ ናቸው። ከእነርሱ ጋር ትቆሚያለሽ? ብዙዎች ያንቋሽሹሻል፥ በሰጠሁሽም **ቃል** ይዘብታሉ፥ አካሄድሽንም ይኮንናሉ፥ ነገር ግን **እኔ** ካንቺ ጋር እሆናለሁ። ብዙዎች በአንቺ ውስጥ የሚናገረውን **ድምጽ** ይንቃሉ፥ ሁሉም **እውነቱን** አያምኑም። ነገር ግን ሌሎች ብዙዎች ያምናሉ። ዋጋውን ትከፍያለሽ፥ ሕዝቤን ወደ **እኔ** ትጠሪያለሽ?*

*የነቢያቶቼ እጅ በእጄ ውስጥ ነው፥ እናም በዚህና በዚያ አቅጣጫ እያዘዋወርኳቸው ነው፥ እናም በምድር ላይ ስፍራ እያስያዝኳቸው (እየመደብኳቸው) ነው። ማስጠንቀቂያውን ያሰማሉ፥ ከዚያም ያየሻቸው ክንውኖች፥ ገናም ያላየሻቸው ተጨማሪ ብዙዎች ይጀምራሉ።"*

እየተናገረ ዓይኖቹ ወደ ልቤ ውስጥ ሲመለከቱ ይሰማኛል። ፍርሀት አልተሰማኝም፥ ነገር ግን በሰውነቴ ውስጥ ያለው ሰዋዊነት ሁሉ ተሰማኝ። ሁልጊዜም **እርሱ** ከእኔ ጋር እንዳለ እንደማውቅ ይሰማኝ ነበር፥ ነገር ግን በዚህ ቅጽበት ውስጥ ሁል ጊዜም በዚህ እውቀት ውስጥ እንዳልተራመድሁ አወቅሁ። እጅግ ብዙ ልሸከምባቸው፥ አልያም ነገሮችን ያለ**ጌታ** ጥበብ ለማድረግ የሞከርኩባቸውን ብዙዎቹን ጊዜያት ማየት እችል ነበር፥ እናም **እርሱ** ትክክል እንደነበር አወቅሁ። **ጌታ** ሙሉ በሙሉ እንዲያስችለኝ፥ አልያም አገልጋዩ እንድሆን ኃይልን እንዲያስታጥቀኝ አልፈቀድሁለትም። ቅንአት ነበረኝ፥ ብዙ ብርታት ግን አልነበረኝም።

**ጌታ** ሆይ፥ ውሰደኝና ተሸከመኝ አልሁት። አገልጋይህ እንድሆንና **ቃልህን** በኃይልህ መናገር እንድችል አስችለኝ። ያለ**አንተ** የሕይወቴ ራስነት ከዚህ የበለጠ ለመሄድ አልችልም። አምንሀለሁ፥ በ**አንተ** ላይም እደገፋለሁ። የ**አንተ** ብርታትና ጥበብ፥ በራሴ አይደለም። ለሕዝባችንም **ልብህን** ስጠኝ፥ እንዳናግራቸውና በ**አንተ** ዓይን እንዳያቸው እርዳኝ። ዋጋውን እከፍላለሁ፥ ከ**አንተ** ውጪ ሌላ አልሻምና። **ጌታ** እጅግ በሀዘኔታ ዓይኖች አየኝ፥ እናም ወደ ልቤ ሰንዝሮ ጎትቶ አወጣው። ደንግጬ ነበር፥ እናም ጮኽኩ። በእርጋታ ፈገግ አለብኝ፥ ከዚያም ወደ **ራሱ** ልብ ደረሰና የራሱን ልብ ጎትቶ አወጣው፥ ከዚያም ለእኔ ሰጠኝ።

እንዲህ አለ፡ “*አሁን የእኔ ልብ አለሽ። ምን እንደምታደርጊበት ተጠንቀቂ። ከንቱ አድርገሽ አትቁጠሪው፥ ምሪቱንም ከመከተል ወደ ኋላ እንዳትይ። በጥንቃቄ ጠብቂው፥ እንዲሁም ለሌሎችም ከመስጠት (*release*) ወደ ኋላ እንዳትዪ። በዙሪያሽ ያሉትን በእኔ ፍቅር ውደጂያቸው፥ እናም እውነቱን ተናገሪ።*” እዛ እንደቆምሁ ምንም ህመም አልተሰማኝም፥ ነገር ግን ቅለት ተሰማኝ። ከዚህ በኋላ አልፈራሁም፥ ድካምም አልተሰማኝም። በጣም ሙላትና ነጻነት ተሰማኝ፥ እናም ሙሉ በሙሉ እንደ ተወደድሁና ምንም ገመድ እንዳልታሰረብኝ ተሰማኝ። በፍቅሩ ቅለትና፥ እርሱን ባለመቀበል ህይወትን እንዴት እንደምናከብዳት በማሰብ ተወስጄ ነበር። ልቡን ለራሴ ወሰድሁ፥ እናም በውስጤ ታላቅ መነሳሳት ነበር። ለእግዚአብሔር ሕዝቦች የሆነ ዓይነት ተስፋ ተሰማኝ። የሚጠብቃቸውን ታላቅ ፍፃሜ አየሁ፥ እንዲሁም ከእርሱ ጋር ዳግም የመገናኘትን ክብር። የመጨረሻው ብድራት ሁሉ የተገባው ነበር። (It was worth it all.)

-ሱዛን ከሚንግስ

ጃንዋሪ 31፥2002 ዓ.ም፥ከጠዋቱ 3፡41

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com